ኤን.ኤች.ኤስ
(ብሔራዊ የጤና ሥርዓት)

የጤና ስርዓቱ በዩኬ ውስጥ እንዴት እንደሚደራጅ



የእንግሊዝ የጤና ስርዓት ኤን.ኤች.ኤስ. በመባል ይታወቃል።



የመጀመሪያ ደረጃ እንክብካቤ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚደረግ ነፃ የጤና እንክብካቤ ነው። የሆስፒታል ጤና እንክብካቤ ሁለተኛ ደረጃ እንክብካቤ ነው። አንዳንድ ሰዎች አገልግሎቱን ለማግኘት ክፍያ መፈጸም ይጠበቀባቸዋል።



ጠቅላላ ሃኪምዎ የማህበረሰብዎ የሕክምና ዶክተር ነው።እነሱ ብዙውን ጊዜ ከነርሶች ፣ ከፊዚዮቴራፒስቶች ፣ ከፋርማሲስቶች ፣ ከስነ-ልቦና ባለሙያዎች እና ከመሳሰሉት ጋር አብረው ይሰራሉ።

እርስዎ በሚኖሩበት አቅራቢያ ከሚገኝ ጠቅላላ ሃኪም ዘንድ መመዝገብ ያስፈልግዎታል።



ጠቅላላ ሐኪምዎ ሊመረምርዎና ሊያከምዎ ይችላል። አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ሆስፒታሉ ውስጥ ወደሚገኝ ስፔሻሊስት ሊመሩዎት ይችላል።

አስቸኳይ እንክብካቤ እና አፋጣኝ እርዳታ ከፈለጉ የአምቡላንስ አገልግሎት እንዲያገኙ የድንገተኛ ጊዜ ቁጥር 999 ይደውሉ።





ከቻሉ ወደ ሆስፒታል የአደጋ እና ድንገተኛ ክፍል (A&E) በቀጥታ መሄድ ይችላሉ።

ለተጨማሪ መረጃ የሚከተለውን ይጎበኙ

www.nhs.uk/live-well/eat-well/
www.doctorsoftheworld.org.uk/

DOCTORS OF THE WORLD

BritishRedCross

የተዘጋጀው በ

POSITIVE NEGATIVES